המשך פעילויות בעקבות הסיפור - የዮ-ዮ እለተ ዓርብ



በ: ዳቲያ ቤን ዶር
ምሳሌዎች: አቭኔር ካጽ
הוֹצָאָה: מודן
የእድሜ ክልል: ቅድመ ትምህርት ቤት

### קְרִיאָה

**ሌላስ ምን?" ለቤተሰባዊ ንባብ የሚሆን ጠቃሚ ምክር"**

በእያንዳንዱ ገጽ መጨረሻ ላይ ክፍት ጥያቄ ወይም ዓረፍተ ነገር የሚተዉ መጽሐፍት አሉ። ስለሆነም ወጣት አንባቢዎች እንዲሳቡ፣ እንዲሳተፉና በሚቀጥለው ገጽ ምን እንደሚጠብቃቸው እንዲገምቱ እድል ይሰጣቸዋል። በማንበብ ጊዜ በገጾቹ መካከል ለአፍታ ቆም ይበሉ፣ ይገምቱ ወይም በሚቀጥለው ገጽ ላይ ምን እንደሚጠብቃቸው አንድ ላይ ያግኙ።

### שִׂיחָה

**ውይይት እንደ ሁሌው እለተ ዓርብ**

ታሪኩን ተከትለን አብረን ማሰብ እንችላለን – በየሳምንቱ ዓርብ ዓርብ ምን ያደርጋሉ? እንዲሁም መደበኛ አዘገጃጀቶች፣ ዝግጅቶች ወይም የቤተሰብ ሥርዓቶች አሉዎት? በተለይ ምን ማድረግ ይወዳሉ? ለሠንበት መቃረቢያ ?ሽር ጉድ ስላሉ ወይም ስለተደሰቱ ሠንበት የበለጠ አስደሳችና ደስ የሚል እንደሆነ ተሰምቶዎት ያውቃል

מִשְׂחָק

**ከምስሎች ጋር መጫዎት**

የአቨነር ካጽ ክላሲክ ሥዕላዊ መግለጫዎች የዮዮ ብዙ ሥራዎችን ያሳያሉ። አንዳንድ ጊዜ አንድ ትልቅ ሐብሐብ ይሸከማል። አንዳንድ ጊዜ በብስክሌት ይጋልባል። አንዳንዴም መታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ይታጠባል። የአካላዊ እንቅስቃሴ ጨዋታ መጫወት ይችላሉ – እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በተራው የመጽሐፉን በዘፈቀደ ይከፍትና በምስሉ ላይ የተገለጸውን በእንቅስቃሴ ያሳያል – ሌሎች የቤተሰብ አባላት ስለ እርሱ አሁን ምን እንዳለ መገመት አለባቸው።

בִּשּׁוּל

**የሠንበት አዘገጃጀት**

የቲማቲም ጭማቂ? የብርቱካን ማርማላታ? ምናልባት የተጠበሰ ፓንኬክ? በታሪኩ ውስጥ ከሚታዩ የተለያዩ ምግቦችና መጠጦች ውስጥ የመጽሐፉን ገፆች ማገላበጥ፣ መምረጥና ማዘጋጀት ይችላሉ። ከዝግጅቱ በኋላ ማረጋገጥ የሚችሉት – ?ፓን ኬኩን ለመሥራት ስንት ድንች ተጠቅመዋል? ማርማላታውንስ ለማዘጋጀት ስንት ብርቱካን

מִשְׂחָק

**የማስታዎስ ጨዋታ**

ታሪኩን ስንት ጊዜ አንብበዋል? የሚያስታውሱትን ለመፈተሽ ጊዜው አሁን ነው! ወንድና ሴት ልጆች አንድን መጽሐፍ ደጋግመው ማንበብ ያስደስታቸዋል። በሚያስታውሱበት ጊዜም በራሳቸው እንዴት እንደሚናገሩ ሲያውቁ በደህንነትና በእርካታ ስሜት ይሞላሉ። ልጆቹን ማስታወስን እንዲያሚሉ የሚያቀርቡላቸው – ስንት ቲማቲሞች? ስንት ብሩሽ? የማስታወስ ችሎታዎን እንዲፈትሹና ስለ ታሪኩ ዝርዝሮች እንዲጠይቁ ይጠቁሟቸው።

הַשְׁרָאָה

**ፒንተረስት**

ተጨማሪ ስራዎች፣ ዘፈኖችና እንቅስቃሴዎች በፒጃማ ቤተ መፃህፍት ፒንተረስት ላይ።

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org